የ2005 ዓ. ም የ20/80 እና 40/60 የቤት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 139/2015

በ2005 ዓ.ም በተደረገው የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ወቅት ተመዝግቦ ከሚጠባበቀው ፈቃደኛ የሆኑ ነዋሪዎች ውስጥ አቅም ያላቸውን በመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበር በማደራጀት ተጠቃሚ ማድረግና የቤት ፈላጊውን ችግር መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ዜጎች በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት ተደራጅተው የቤት ችግራቸውን ለመቅረፍ እንዲችሉ እና ተጠቃሚ ለማድረግ የተቀመጠውን መመዘኛ ሊያሟሉ የሚችሉትን ቤት ፈላጊዎች ግልፅ፣ ተደራሽ፣ አሣታፊ፣ ያልተገባ ተጠቃሚነት በመከላከል ተጠያቂነት የሰፈነበት የአሰራርና የአደረጃጀት ሥርዓት መፍጠር በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል (ሠ) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2005 ዓ.ም የ20/80 እና 40/60 የቤት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 139/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. "**አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. "**አዋጅ**" ማለት እንደ አግባብነቱ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 985/2009 ወይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 ነው፤
4. "**ቢሮ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ነው፤
5. "**ኤጀንሲ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ ሲሆን እስከ ወረዳ ያለውን ጽህፈት ቤት ይጨምራል፤
6. "**አደራጅ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ ወይም እሱ የሚወክለው የአስተዳደሩ ተቋም ነው፤
7. "**የኅብረት ሥራ ማኅበር**" ማለት በኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ መመሪያ መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ የጋራ ህንፃ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፤
8. "**ዝግ ሂሳብ**" ማለት የመኖሪያ ቤት ለመሥራት በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስም ቅድሚያ የሚጠበቅበትን የቤቱን ግንባታ ወጪ በባንክ ለማስቀመጥ የሚከፈት የማይንቀሳቀስ የቁጠባ ሂሳብ ነው፤
9. "**ባንክ**" ማለት የኅብረት ስራ ማኅበራቱ ገንዘባቸዉን በማይንቀሳቀስ የቁጠባ ሂሳብ ለማስቀመጥ ወይም ሌሎች የባንክ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚመርጡት ማንኛውም ባንክ ነው፤

10. **"የቤት ልማት ፕሮግራም"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ አስተባባሪነት የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመቅረፍ የተዘጋጀ የ20/80፣ 40/60 እና የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፤

11. **"የለማ መሬት"** ማለት መሠረተ ልማት የተሟላለት መሬት ነዉ፤

12. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. **የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ በ2005 ዓ.ም የ20/80 እና በ40/60 የቤት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች በጋራ ህንጻ መኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበር ቤት ለመገንባት ፈቃደኛ ሁነው ለሚደራጅና ለተደራጀ እና ይህን መመሪያ በሚያስፈጽም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. **ዓላማ**

በቤት ልማት ፕሮግራም ከተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች አቅምና ፍላጎት ያላቸው በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተደራጅተው ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን በማቀናጀት የቤት ችግሮቻቸውን በጋራ ጥረት ሊፈቱ የሚችሉበትን አማራጭ መፍጠር፡፡

6. **መርህ**

በአዋጁ የተጠቀሱት የኅብረት ሥራ ማኅበራት መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. መሥፈርቱን መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ግልጽና አሳታፊ እና የተጠያቂነትን አሰራር ማስፈን፤
2. የመኖሪያ ቤት ችግርን በራስ አቅም ለመፍታት የሚደረግ የእውቀት፣ የሀብትና ጉልበት አስተዋጽዖን የሚደግፍና የሚያበረታታ አቅጣጫ መከተል፡፡

ክፍል ሁለት

የሕብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት

7. **የምዝገባ መስፈርቶች**

የአባልነት ምዝገባ መስፈርቶች በኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ለዚህ የቤት ልማት ፕሮግራም አፈጻጸም ሲባል፡-

1. በ2005 ዓ.ም በቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለመሆን ተመዝግበው ስማቸው በምዝገባ መረጃ ቋት ውስጥ የሚገኙና በኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅተው

በራሳቸው አቅም ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያላቸውና የቁጠባ ደብተር ሂሳብ ያልዘጉ፤

2. በማህበር ቤት ለመገንባት ተመዝጋቢ ሆኖ ከቤት ግንባታ ወጪ ቅድሚያ ክፍያ 70 በመቶ በህብረት ስራ ማህበሩ ስም በባንክ በሚከፈተው ዝግ ሂሳብ ማስቀመጥ የሚችል፤
3. በቤት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን በ2005 ዓ.ም የተመዘገበ ከሆነ ቦታ ተረክቦ የግንባታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ከምዝገባ የተሰረዘ መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤
4. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በራሱም ሆነ በትዳር አጋሩ ስም ቤት ወይም ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ከ1997 ዓ.ም ወዲህ በስጦታ ወይም በሽያጭ ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፤
5. የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ሆኖ ለመደራጀት እንደምዝገባው ዐይነት ባለ 3 መኝታ ቤት፣ ባለ 2 መኝታ ቤት እና ባለ 1 መኝታ ቤት በሚል እንደ ቤት ዓይነቱ ለመደራጀት ፈቃደኛ የሆነ፤
6. የከተማ አስተዳደሩ ያወጣቸውን የግንባታ ሕጎች በማክበር በኅብረት ሥራ ማህበሩ አማካኝነት ከአባላቱ ጋር በጋራ ህንፃ የመኖሪያ ቤት ለመገንባት የተስማማ፤
7. ማንኛውም ተደራጅ ቢሮው በሚያዘጋጀው የህንጻ ዲዛይን ሳይት፣ ብሎክ፣ የህንጻ ወለል እና የቤት አቀማመጥ በዕጣ ለመደልደል ፈቃደኛ የሆነ፤
8. በፕሮግራሙ ተካቶ ቤት የሚገነባ ቤት ፈላጊ የህንጻ ግንባታው ሳይጠናቀቅ በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የማይችል መሆኑን የሚቀበል፤
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አባል በሞት ምክንያት ሲለይ በሕግ አግባብ ተረጋግጦ ለሚቀርበው ወራሽ የህንጻ ግንባታው ከመጠናቀቁ በፊት ሊተላለፍ ይችላል፡፡

8. <u>ስለምዝገባ</u>

1. ቤት ፈላጊ የቤት ፍላጎቱን ቀደም ሲል በተመዘገበበት የቤት ዓይነት መሠረት ቢሮው በዕጣ በሚደለድለው የጋራ ህንጻ መኖሪያ ማኅበር ውስጥ ለመደራጀት የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ በማቅረብ ስምምነቱን ለቢሮ ያሳውቃል፤
2. የቤት አይነት ምርጫ ያከናወነ እና በማኅበር ለመደራጀት ዕጣ የወጣለት ተደራጅ ዝርዝር መረጃ ቢሮው ለአደራጁ ይልካል፤
3. ተመዝጋቢዎች በማህበር ለመደራጀት አደራጁ ጋር ለምዝገባ ሲቀርቡ የቤት ፍላጎት ምዝገባ ቅጻ-ቅጾች ይዘው ይቀርባል፡፡

9. <u>በኅብረት ስራ ማኅበር የሚደራጁ አባላት ብዛት</u>

1. በአንድ ህንጻ አንድ ኅብረት ሥራ ማኅበር ይደራጃል፣ የአባላቱ ብዛት በህንፃ ዲዛይን፣ በሀንጻው ከፍታና በቤት ዓይነት የሚወሰን ሆኖ ዲዛይኑ በመኝታ ቤት ዓይነት ስብጥር የአባላት ብዛት እንደመነሻ በB+G+9-90፣ በ2B+G+12-110፣ በ2B+G+13-120 እና በ2B+G+15-140 ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ማስተር ፕላን በሚፈቅደው መሠረት የግንባታው ከፍታና ጥግግት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ስለ ቤቶች አሠራር፤ ዐይነትና የግንባታ ዋጋ</u>

10. <u>ስለቤቶች አሰራር</u>

1. የከተማ አስተዳደሩ በሚያዘጋጀው መሬት ላይ የሚገነባው የጋራ መኖሪያ ህንጻ የአካባቢውን ልማትና የከተማውን ማስተር ኘላን እንዲሁም የከተማ ህንፃ ጥግግትና ከፍታ መሠረት ያደረገ ይሆናል፣
2. የከተማ አስተዳደሩ አማራጭ የህንጻ ዲዛይን የሚያቀርብ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት በአማራጭ ከቀረበው የህንፃ ዲዛይን የተለየ ዲዛይን የከተማዉን ማስተር ፕላን በጠበቀ መልኩ በራሳቸው መርጠው የማሰራትና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አጸድቀው የመጠቀም መብት አላቸው፣
3. የቤቶቹ ግንባታ የሚከናወነው ማህበራቱ በመረጡት የህንፃ ስራ ተቋራጭና አማካሪ ይሆናል፤
4. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ልምድ ያላቸውን ተቋራጮች፣ አማካሪ እንዲሁም ማህበራት ዝርዝር ለማህበራቱ ሊያቀርብ ይችላል፤

5. በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ማስተር ፕላን በሚፈቅደው መሠረት እና የአካባቢውን ደህንነትና ልማት ከግምት በማስገባት ዜሮ እና አንደኛ ወለሎች ለተለያየ አገልግሎት ማዋል ይቻላል፡፡

11.<u>የቤቶች ዓይነት</u>

1. በሚዘጋጀው የህንፃ ዲዛይን መሠረት የሚገነባው የህንፃ ከፍታ እንደመነሻ B+G+9፣ 2B+G+12፣ 2B+G+13፣ 2B+G+15 እና ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አማራጭ ዲዛይኖችን ሊያቀርብ ይችላል፤
3. ቢሮው ባሰራው የአማራጭ ዲዛይን መሠረት በስብጥር የቤት የሚገነቡ ቤቶች ስፋት አማካይ ባለአንድ መኝታ ቤት 60 ካ.ሜ፣ ባለሁለት መኝታ ቤት 75 ካ.ሜ እና ባለሦስት መኝታ ቤት 105 ካ.ሜ ይሆናል፡፡

12.<u>ስለቤቶች ግንባታ ዋጋ ግምት</u>

1. የቤቶች ግንባታ መነሻ ዋጋ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ አንድ ሰንጠረዥ የተመላከተው ይሆናል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም የቤቶች ግንባታ ዋጋ እንደወቅቱ ሁኔታ ሊሻሻል ይችላል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ተግባር፤ ተግባርና ኃላፊነት</u>

13.<u>የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት</u>

ቢሮው በአዋጁ የተሰጡት ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሁኖ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት በ20/80 እና በ40/60 ከተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች መካከል በፍላጎት ወደጋራ የመኖሪያ ህንጻ ህብረት ሥራ ማህበር የሚመጡትን ተመዝጋቢዎች 2005 ዓ.ም በተመዘገቡበት ወይም እንደ አዲስ በመረጡት የቤት ዓይነት ይመዘግባል፤
2. ለጋራ መኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር አገልግሎት የሚውል የለማ መሬት ከመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጠይቆ የመረከብ፤
3. ቢሮው በጥቅል የተረከበውን የለማ መሬት ለአንድ ማኅበር የሚውለውን ቦታ ልዩ ስም ወይም ኮድ በመስጠት ለእያንዳንዱ ማህበር በዕጣ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

4. ቢሮው በ2005 ዓ.ም በ20/80 እና 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች ውስጥ በጋራ የህንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅተው ቤት ለመገንባት የተመዘገቡትን በዕጣ ድልድል የሚያደርግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ እንደሚከተለው ተጠቃሚ ያደርጋል፡-

   ሀ) ለሴት ተመዝጋቢዎች ቅድሚያ 30 በመቶ፤

   ለ) ለአካል ጉዳተኞች 5 በመቶ ፤

5. ዕጣ የወጣላቸው ተመዝጋቢዎች በተደለደሉበት ቦታ የሚጠበቅባቸውን መስፈርት አሟልተው በኅብረት ሥራ ማኅበር እንዲደራጁ ዝርዝራቸውን ለአደራጁ ያስተላልፋል፤

6. ዕጣ የወጣለት ተመዝጋቢ መሬት ከመሰጠቱ በፊት ከሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራም በጋራ መኖሪያ ህንጻ ኅብረት ሥራ ማኅበር ለመደራጀት የተመዘገቡትን ተጠቃሚዎች ከ20/80 እና ከ40/60 ፕሮግራም መሰረዙን የሚገልፅ ማስረጃ ይሰጣል፣

7. ለጋራ መኖሪያ ህንጻ ኅብረት ሥራ ማኅበር በዕጣ የተላለፈላቸው ቦታ እንዲከለል ወይም እንዲሸነሸን እንዲሁም የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲዘጋጅላቸው በአዋጁ ስልጣን ለተሰጠው አስፈጻሚ አካላት መረጃውን ያስተላልፋል፤

8. የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በተደራጁበት ዓላማ መሠረት ግንባታ እንዲያከናውኑ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

9. በጋራ የህንጻ መኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ ቤት ፈላጊዎችን ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤ ዝዝራቸውን ለአደራጁ ይልካል፤

10. በዝግ የባንክ ሂሳብ የተቀመጠውን ገንዘብ ለማስለቀቅ እንዲቻል ግንባታው የደረሰበትን ደረጃና በየደረጃው የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን እንዲለቀቅ ለአደራጁ ያሳውቃል፤

11. በዚህ አንቀጽ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያውን በተገቢው ለማስፈጸም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በመቀናጀት ይሰራል፡፡

14. <u>ለጋራ ህንጻ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኅበር የሚመዘገቡ ሰዎች ግዴታ</u>

1. የጋራ ህንጻ የቤት ስራ ማህበር ለመደራጀትና ለመመዝገብ የሚፈልግ ማንኛውም ተደራጅ ይህን መመሪያ የማክበር፤

2. ማንኛውም አባል የጋራ ህንጻ የቤት ስራ ማኅበር ለመደራጀትና ምዝገባ ለማካሄድ በቅድሚያ በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት በግንባር ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካይነት ፍላጎቱን ለቢሮው ማቅረብ፤

3. በኅብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት የሚፈልግ ሰው መብቱን በሽያጭም ሆነ በስጦታ ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የሚችለው የቤቱ ግንባታ ከተጠናቀቀ ከአምስት ዓመት በኋላ መሆኑን ስምምነት መግባት፤
4. የቤቶቹ ግንባታ ሲጠናቀቅ በቦታው በመገኘት የጋራ ህንጻ የቤት ስራ ማኅበሩ አማካኝነት አባሉ ወይም ሕጋዊ ወኪል በተገኙበት በእጣ የሚደርሰውን ቤት መረከብ፡፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15.ክልከላ

1. ፍቃደኛ ሆኖ በጋራ ሕንጻ የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ተደራጅቶ የነበረ የማህበር አባል ወደ 2005 ምዝገባ ቋት ውስጥ መመለስ አይችልም፡፡
2. በ2005 ዓ.ም የ20/80 እና 40/60 ቤት ልማት ፕግራም ተመዝገቢዎች መካከል በጋራ ሕንጻ የመኖሪያ ቤት በኅብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት በሚደረገው ልየታና ምዝገባ ሂደት አድሎ መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

16.ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

1. በዚህ መመሪያ አፈጻጸም ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን በጽሁፍ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ቅርብ ኃላፊ ቅሬታ ስነሳው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፤
2. ቅሬታ የቀረበለት የሥራ ኃላፊ ለቀረበለት ቅሬታ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣል፤
3. በሥራ ክፍሉ በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ተገልጋይ ጉዳዩን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ኮሚቴውም የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በሶሰት የሥራ ቀናት ውስጥ ለቢሮ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
4. የቢሮው ኃላፊ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በመመርመር በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

17.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

18.ስለተጠያቂነት

ማንኛውም የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ ሰው አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

19.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የቢሮው መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

20.መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ ቢሮው ሊያሻሽል ይችላል፡፡

21.የተሻረ ህግ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ በ2005 ዓ.ም በ20/80 እና በ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች በጋራ ህንፃ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር በመደራጀት የቤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

22.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ያስሚን ውሃብረቢ

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ

<u>የቤቶች ግንባታ ዋጋ ግምት ሰንጠረዥ ለመጀመሪያ ዙር ምዝገባ የቀረበ (በየሩብ ዓመቱ ሊቀየር የሚችል)</u>

<u>የቤቶች ግንባታ ዋጋ ግምት ሠንጠረዥ (1)</u>

ተራ ቁጥር	የህንፃው ዓይነት	የቤቱ ስፋት በሜ/ካሬ	የአንድ ሜ/ካሬ ዋጋ	ጠቅላላ የቤቱ የግንባታ ዋጋ	በአንድ ወለል የመኘታ ቤት ብዛት
1	B+ G+9	60	12,061.90	882,086.75	1
		75		1,104,025.71	3
		105		1,547,300.53	3
4	2B+G+13	60	13,086.82	926,023.38	2
		75		1,157,529.23	6
		105		1,620,540.92	2